በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የተማሪ መማሪያ መጽኃፍትና የመምህሩ መምሪያ ለሚያዘጋጁ የወጣ የመምረጫ መስፈርት

1. በሚያዘጋጀው የትምህርት አይነት ላይ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው፤
2. በአሁኑ ሰዓት በቀጥታ የትምህርት አይነቱን በብቃት እያስተማሩ ያሉ፤
3. በሚያስተምሩት የትምህርት አይነት 10 ዓመትና በላይ አገልግሎት ያላቸው፤
4. በተመሩቀበት የትምህርት አይነት ውጤት/CGPA/ 2.5 እና በላይ ያላቸው
5. ስርአተ ትምርቱን የገመገሙና ከስርዓተ ትምህርት ኮሚቴ ስለ **ትክክለኛነቱ** ማረጋገጫ የተሰጣቸው
6. በመማር ማስተማሩ ዙሪያ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር አድርገው እውቅና የተሰጣቸውና ጥናቱን ማቅረብ የሚችሉ፤
7. በፔዳጎጂና በካሪኩለም የትምህርት መስክ ዙሪያ አጫጭር እና የረጅም ጊዜ ስልጠና የወሰደ/የወሰደች
8. የሚያስተምሩት የትምህርት ይዘት በጥልቀት የተረዱ፤ በማስተማር ስነ ዘዴ ብቃትና እውቀት ያላቸው፤ የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በመረዳት ተግባራዊ ያደረጉ እና በተማሪ ውጤት ላይ መሻሻል ያመጡ
9. ቀደመ ብሎ በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ላይ የተሳተፉ ወይም ያዘጋጁ ወይም የአርትኦት ስራ የሰሩ፤
10. ስርአተ ትምህርቱን ለማበልጸግ አጋዥ መጽሃፍ ወይም ማኑዋል ያዘጋጁ፤
11. የመምህር ሙያ ፍቃድ ያላቸው፤
12. በስነ ምግባሩ ለሌሎች አርዓያ የሆኑ፤ ሃላፊነት የሚሰማቸዉ፤ የሙያ ክብርና ስነ ምግባር ያላቸዉ፤
13. የሚያዘጋጀውን የትምህርት ማስተማሪያ ቋንቋ አራቱ ክህሎት ያሉት፤
14. የ 2011 ዓ.ም 2 ኛ መንፈቅ አመት፤የ 2012 ዓ.ም ሙሉ ዓመትና የ 2013 ዓ.ም የመጀመሪያ መንፈቅ አመት የውጤት ተኮር አማካይ ውጤት

ማጠቃለያ

1. የተመረጡ አዘጋጆች ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርት በአባሪነት በማስቀመጥና የግል ማህደረ ተግባራቸውን /personal portfolio/ ይደራጃል። ተወዳዳሪዎችም ያደራጁት የግል ማህደረ ተግባራቸውን ከትምህርት ቤቱ የተረጋገጠ መሆን አለበት።
2. ለእያንዳንዱ መስፈርት ተገቢው መረጃ እና ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል።

የግል ማህደረ ተግባት መካተት/መደራጀት/ የሚገባቸው

- የውጪ ሽፋን
  - ✓ ሙሉ ስም
  - ✓ የትምህርት ደረጃ፣አይነት
  - ✓ የሚያስተምሩበት የትምህርት ቤቱ ስም
- ማውጫ
- የመጀመሪያ ገጽ ውስጥ

- ካሪኩለም ቪቴ
  - ቀጣይ ገጾች ላይ
- መግቢያ
- መረጃና ማስረጃ በቅደም ተከተል በመስፈርቱ
  - ሌሎች ከመስፈርቱ ውጪ ወሳኝ መረጃዎች
  - ማጠቃለያ

የኮሚቴ አወቃቀርን በተመለከተ

በክፍለ ከተማ ደረጃ

- የዕህፈት ቤት ሃላፊ
- የመምህራን ልማት ቡድን መሪ
- የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት እና ግምገማ ቡድን መሪ
- የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት እና ግምገማ ቡድን መሪ(አፋን ኦሮሞ)
- የክፍለ ከተማ መሰረታዊመምህራን ማህበር
- የሱፐርቫይዘር አስተባባሪ

በትምህርት ቤት ደረጃ

- የት/ቤቱ ርዕሰ መምክር
- የመ/ማ/ም/ር/ መምህር
- የመ/ል/ም/ር/መምህር
- የመምህራን ማህበር
- የትምህርት ክፍል ተጠሪዎች
- የክላስተር ሱፐርቫይዘር/አስተባባሪ

ማሳሰቢያ፡-

- **ቀድሞ ስቴቲክስ የትምህርት አይነት ወደ ቪዡዋል አርት በመቀየሩ ይህን የትምህርት አይነት የመፅሃፍት ዝግጅት የሚሰሩ መምህራን በተዛማጅ የትምህርት አይነት ማለትም ሙዚቃ ስቴቲክስ ሆነው በመስፈርቱ መሰረት የመጀመሪያ ዲግሪ እና በላይ መሆን ይጠበቅበታል**
- **መረጃ የሚፈልጉ መለኪያዎች በአጠቃላይ በየ ደረጃው ያለ ኮሚቴ ያፀደቀው መረጃ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል**
- በመስፈርቱ መሰረት ከተወዳደሩ መምህራን መካከል በድምር ውጤት 50 እና በላይ ያመመጡ መምህራን ብቻ ተወዳዳሪ ይሆናሉ

አባሪ

መለኪያ	**የተሰጠው ክብደት**	**መግለጫ**	

በሚያዘጋጀው የትምህርት አይነት ላይ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው፤	5		
በአሁኑ ሰዓት በቀጥታ የትምህርት አይነቱን በብቃት እያስተማሩ ያሉ፤	5		
በሚያስተምሩት የትምህርት አይነት 10 ዓመትና በላይ አገልግሎት ያላቸው፤	15		
በተመሩቀበት የትምህርት አይነት ውጤት/CGPA/ 2.5 እና በላይ ያላቸው	20	**የመመረቂያ ነጥብ** /CGPA/*5	
ስርአተ ትምርቱን የገመገሙና ከስርዓተ ትምህርት ኮሚቴ ስለ **ትክክለኛነቱ** ማረጋገጫ የተሰጣቸው	5		
በመማር ማስተማሩ ዙሪያ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር አድርገው እውቅና የተሰጣቸውና ጥናቱን ማቅረብ የሚችሉ፤	5		
በፔዳጎጂና በካሪኩለም የትምህርት መስክ ዙሪያ አጫጭር እና የረጅም ጊዜ ስልጠና የወሰደ/የወሰደች	5		
የሚያስተምሩት የትምህርት ይዘት በጥልቀት የተረዱ፤ በማስተማር ስነ ዘዴ ብቃትና እውቀት ያላቸው፤የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በመረዳት ተግባራዊ ያደረጉ እና በተማሪ ውጤት ላይ መሻሻል ያመጡ	5		
ቀደመ ብሎ በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ላይ የተሳተፉ ወይም ያዘጋጁ ወይም የአርትኦት ስራ የሰሩ፤	3		
ስርአተ ትምህርቱን ለማበልጸግ አጋዥ መጽሃፍ ወይም ማኑዋል ያዘጋጁ፤	5		
የመምህር ሙያ ፍቃድ ያላቸው፤	5		
በስነ ምግባሩ ለሌሎች አርዓያ የሆኑ፤ ሃላፊነት የሚሰማቸዉ፤ የሙያ ክብርና ስነ ምግባር ያላቸዉ፤ ምንም ዓይነት የዲሲፒሊን ግድፈት የሌለባቸው	5		
የሚያዘጋጀውን የትምህርት ማስተማሪያ ቋንቋ አራቱ ክህሎት ያሉት፤	2		
የ2011 ዓ.ም 2ኛ መንፈቅ አመት፤የ2012 ዓ.ም ሙሉ ዓመትና የ2013 ዓ.ም የመጀመሪያ መንፈቅ አመት የውጤት ተኮር አማካይ ውጤት	15	**የአራቱ ሴሚስተር አማካይ የውጤት***0.15	
ድምር	100		